DENVER PUBLIC SCHOOLS | Academics

# ተማሪዎችን በቤት ውስጥ መደገፍ 2ኛ ክፍል

*በመጀመሪያ በሃዋርድ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች የተዘጋጀ እና ለዴንቨር የሕዝብ ት/ቤቶች እንዲስማማ ተደርጎ የተወሰደ*

## አጭር መግለጫ

ይህ መመሪያ ት/ቤቶች በCOVID-19 ምክንያት በተዘጉበት ወቅት ተማሪዎች በትምህርት ተግባሮች ላይ እንዲቆዩ ለማድረግ ሀሳቦችን እንዲሰጥ የተዘጋጀ ነው። የተዘረዘሩት ተግባራት ልጆቻችን በቤታቸው በሚውሉበት ጊዜ በአዕምሯቸው ንቁ ሆነው እንዲቆዩ ለመርዳት የታሰቡ ናቸው። የተግባር ሀሳቦቹ በት/ቤቶች የሚሰጠውን የመጀመሪያ ደረጃ የመማር-ማስተማር ሂደትን አይወክሉም። የመጀመሪያ ደረጃ የመማር-ማስተማር ምርጥ ተሞክሮዎች ተማሪዎች ወደ ት/ቤት በሚመለሱበት ጊዜ የሚታዩ ናቸው።

ልጆች በቤታቸው የሚያከናውኗቸው ተግባሮችና ሥራዎች እንደምዘና አገልግሎት የሚውሉ ወይም ወደ ተማሪዎች ውጤቶች (ግሬድስ) የሚቆጠሩ አይሆኑም። ቤተሰቦች ከዚህ በታች ያለውን ዝርዝር አንብበው ጠቃሚና ተደራሽ የሆኑ አማራጮችን መምረጥ ይኖርባቸዋል። ተግባራቱ ከአንድ ጊዜ በላይ ሊሠሩ ይችላሉ።

## ለምሳሌ የቀረበ የየዕለት ጊዜ ሰሌዳ

| | | |
|---|---|---|
| 8:00-9:00 | **መንቃት እና መዘጋጀት** | ቁርስ መብላት፣ መልበስ እና ለቀኑ መዘጋጀት |
| 9:30-10:00 | **የትምህርት ሰዓት** | ከዚህ በታች ካለው ዝርዝር ውስጥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ አማራጮን ምረጡ። |
| 10:30-11:30 | **የስክሪን (የቲቪና ሞባይል) ጊዜ** | ከዚህ በታች ካለው የስክሪን-ተኮር ተግባሮች ዝርዝር ውስጥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ምረጡ። |
| 11:30-12:30 | **ምሣ እና ነፃ ጊዜ** | ምሣ ብሉ፣ ለእግር መንገድ ወይም ውጭ ለመጫዎት ሂዱ |
| 12:30-1:30 | **ንባብ** | አንድ መጽሐፍ ማንበብ ወይም ከዚህ በታች ካሉት አቅርቦቶች አንድ የኦንላይን መጽሐፍን ምረጡና አንብቡ። |
| 1:30-3:00 | **የትምህርት ሰዓት** | ከዚህ በታች ካለው ዝርዝር ውስጥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ አማራጮችን ምረጡ። |

| 3:00-4:00 | **ነፃ ምርጫ** | እንደ ሌጎስ፣ ስዕል፣ ምግብ ማብሰል፣ ፐዝሎች፣ የቦርድ ላይ ጨዋታዎች ያለ ተግባርን ምረጡ። |
|---|---|---|

# የትምህርታዊ ተግባር ምርጫዎች

እያንዳንዱ የትምህርት ዘርፍ "የምርጫ ቦርድ" አማራጮች አሉት። በእያንዳንዱ ቀን ከተወሰኑ የትምህርት ዘርፎች የተለያዩ ተግባራትን ለመምረጥ ሞክሩ። እነዚህ አማራጮች የአካላዊ እንቅስቃሴ፣ የመጽሐፍት ንባብ፣ እና የቴክኖሎጅ ጠቀሜታ፣ የመስመር-ላይ አቅርቦቶችን/ግብዓቶችን እና የቴሌቪዥን ፕሮግራም ዕድሎችን ያካትታሉ። ልጆችዎ ስለሚሠሯቸው ተግባራት ከልጆችዎ ጋር መነጋገር የንግግር ክህሎቶቻቸውን እና ግንዛቤያቸውን ለማጠናከር ይረዳል።

ልጆችዎ በየቀኑ የተለያዩ ተግባራትን እንዲመርጡ እና በሁሉም የትምህርት ዘርፎች ቀጣይነትን ለማበረታታት የሚከተለውን ሠንጠረዥ ተጠቀሙ (ከሃዋርድ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች የተገኘ እና ለዴንቨር የሕዝብ ት/ቤቶች እንዲስማማ ተደርጎ የተወሰደ):-

| ርዕስ | አማራጭ 1 | አማራጭ 2 | አማራጭ 3 | አማራጭ 4 |
|---|---|---|---|---|
| **የቋንቋ ጥበባት** | አንድን ታሪክ ካነበባችሁ በኋላ ዋና ገጸ-ባሕሪውን እና ችግሮችን ለማቃለል የወሰዳቸውን/የወሰደቻቸውን እርምጃዎች ሳሉ። ሥራችሁን ለአንድ ጓደኛ ወይም የቤተሰብ አባል አሳዩ። | ስለአንድ የዕለቱ ቃል አስቡ። አንድ ወረቀትን ወደ 4 ክፍሎች እጠፉት።<br><br>1. ቃሉን ጻፉ።<br>2. ቃሉን ተርጉሙት።<br>3. ቃሉን በስዕል አሳዩ።<br>4. ቃሉን በ0. ነገር ውስጥ ተጠቀሙት።<br><br>ወረቀቱን ዘርጉ እና የቤተሰብ አባላት ቃሉን በንግግራቸው ውስጥ ምን ያህል ጊዜ እንደሚጠቀሙበት ቁጠሩ (ታሊ አድርጉ)። | የሚስባችሁን ኢ-ልብወለድ መጽሐፍ ምረጡ። ካነበባችሁት በኋላ መጽሐፉን በማንበብ የተማራችኋቸውን 5 እውነታዎችን ጻፉ። እውነታዎቹን በስዕል ግለጹ። | የተዘበራረቁ ቃላት የመገጣጠም ጨዋታን ተጫወቱ። 50 የወረቀት ካሬዎችን ቆራርጡ እና በእያንዳንዱ ካሬ ላይ አንዳንድ ፊደሎችን ጻፉ። ለእያንዳንዱን ቫውል (a,e,i,o,u) እና ለተለመዱት ኮንሶናንቶች (l,m,n,s,t,r) በርካታ ቅጅዎችን አዘጋጁ። ሰባት ፊደሎችን ምረጡ እና ፊደሎችን የቻላችሁን ያህል ብዙ ቃላትን ለመሥራት ተጠቀሙባቸው። |
| **ሒሳብ** | እንደ ጠረጴዛ፣ መጽሐፍ፣ የጥርስ ቡርሽ፣ ወዘተ ያሉ የተለያዩ ነገሮችን ርዝመቶች ገምቱ። ከዚያ ማስመሪያን በመጠቀም ለኳቸው እና ግምታችሁን ከትክክለኛዎቹ | አንድ ባለሦስት አኃዝ ቁጥር ጻፉ። በቁጥር መስመር ላይ አሳዩ። ከዚያ ቁጥር የሚበልጡ ወይም የሚያንሱ ቁጥሮችን ጻፉ። ከመረጣችሁት ቁጥር በ10 የሚበልጥ፣ በ10 የሚያንስ፣ በ100 | ሁለት ባለሁለት አኃዝ ቁጥሮችን ለመሥራት የመጫዎቻ ካርታዎችን ተጠቀሙ። እነዚያን ቁጥሮቹን ደምሩ። እንዴት እንደደመራችኋቸው አሳዩ። | ጥቂት ሳንቲሞችን አንሱ። ሳንቲሞቹን በዓይነታቸው ለዩ እና ድምራቸውን አግኙ። በሁለት እጃችሁ ቆንጥራችሁ ወይም ሌላ ሰው ቆንጥሮላችሁ እንደገና |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ልኬቶች ጋር አወዳድሩ። | የሚበልጥ እና በ100 የሚያንስ ቁጥሮችን ጻፉ። | | ሞክሩት። |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **ሳይንስ** | የቤት የሳይንስ መዋዕል (ጆርናል) አዘጋጁ! በእያንዳንዱ ቀን በጽሑፍ ወይም በስዕል መዋዕልን አክሉ። ምን አስገረማችሁ? ምን ታዘባችሁ (አያችሁ፣ ሰማችሁ፣ ተሰማችሁ)?<br>አንድ ኢ-ልብወለድ የሆነ የሳይንስ መጽሐፍ አንብቡ እና ስለተማራችሁት አዲስ ነገር ጻፉ። | በቤታችሁ ውስጥ የቤት እንስሳ (ፔት) ወይም የእንስሳ አሻንጉሊት አላችሁ? የተቻላችሁን ያህል ዝርዝር በመጠቀም ስለእንስሳው የሰውነት ክፍሎች እና ስለእያንዳንዱ የሰውነት ክፍል ጥቅም ስዕል ስላችሁ በስዕሉ ላይ አመልክቱ (ሌብል አድርጉ)።<br><br>ለቤት ውጪ አንዳች እንስሳትን ታያላችሁ? ምን እያደረጉ አያችዋቸው? ስለሚያደርጉት ነገር ጻፉ። ምን ባሕሪን አያችሁ? | ምክንያትና ውጤቱን አስቡት። አንድን ኳስ የተለያዩ ስፍራዎች (surfaces) ላይ ብታንከባልሉት ምን የሚሆን ይመስላችኋል? ከዳገት ወይም ቁልቁለት ወደ ላይ ወይም ወደ ታች ብትገፋት ወይም ብታንከባልሉት ምን ይሆናል? እንዲያ እንዲሆን ያደረገው ምንድን ነው? ሌላ ምን አሻንጉሊቶችን በተለያዩ መንገዶች መግፋት ወይም መጎተት ትችላላችሁ? ስለምክንያቱና ውጤቱ በቤት የሳይንስ መዋዕላችሁ ላይ ጻፉ። | *በአዋቂ ፈቃድ* በቤታችሁ ዙሪያ ወይም በማኅበረሰባችሁ ውስጥ ደንጋዮችን እና በተክሎች ውስጥ አፈሩን ተመልከቱ። ስንት ዓይነት የተለያዩ ድንጋዮች እና የአፈር ዓይነቶች ማግኘት ትችላላችሁ? እነሱን ለመግለጽ (ቀለም፣ ገጽታ፣ መጠን፣ ቅርጽ) ስንት ቃላት መጠቀም ትችላላችሁ? በቤታችሁ የሳይንስ መዋዕል ውስጥ የደንጋዮችን እና የአፈር ዓይነቶቹን ሳሉና አመልክቱ (ሌብል አድርጉ)። ከዚያም ቀለማቸውን፣ ገጽታቸውን፣ ሽታውን፣ ወዘተ አካታችሁ በጽሑፍ ግለጿቸው። |
| **ሶሻል ስተዲስ** | አንድ ሞዴል ዜጋ በሥራ ላይ ሆኖ/ሆና ሳሉ። ሁኔታዎችን ለመግለጽ ካፕሽኖችን እና ሌብሎችን ተጠቀሙ። | የምትወዱትን ቦታ (የመጫወቻ ቦታ፣ ቤት፣ ማኅበረሰብ) ካርታን ሥሩ። ለካርታውም እንደ ርዕስ፣ ኮምፓስ እና ማውጫ ቁልፍ ያሉ ዝርዝሮችን አክሉ። | ያለፈ ጊዜን እና የአሁን ስዕሎችን ተመልከቱ። ምን ተመሳሳይ እና ምን ልዩ እንደሆነ ተወያዩ። | በተራ ፍላጎቶች እና በመሠረታዊ ፍላጎቶች መካከል ያሉትን ልዩነቶችን ተወያዩ/አስረዱ። ስዕሎችን ሳሉ ወይም ከመጽሔት/ዜና መጽሔት ስዕሎችን ቆርጣችሁ አውጡና ከዚያም በተራ ፍላጎቶች እና በመሠረታዊ ፍላጎቶች ለዩአቸው። |
| **ተያያዥ ሥነ-ጥበባት** | *ሥነ-ጥበብ፡-* የምትወዱት እንስሳ (እንደ ሕጻን ሻርክ ያለ) የልደት ኬክ ወይም የምትወዱትን ምግብ እየበላ ሳሉ። | *ሥነ-ጥበብ፡-* እራሳችሁን እንደ ጀግና (ሱፐርሂሮ) ወይም እንደ አስፈሪ ሰው አድርጋችሁ ሳሉ። | *የሰውነት ማጎልመሻ (PE) እና ጤና፡-* የመረጣችሁትን የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ለ30 ደቂቃ ሥሩ። | *ሙዚቃ፡-* የተለያዩ የቤት ውስጥ እቃዎችን በመጠቀም የተለያዩ ምቶችንና ዜማዎችን ፍጠሩ። |

## ዲጅታዊ መረጃዎች

*በዲጅታዊ መንገድ ሊገኙ የሚችሉ የተወሰኑ ግብዓቶች እዚህ ይገኛሉ፦*

- Scholastic Learn at Home
- PBSKids
- የዴንቨር የሕዝብ ት/ቤቶች ዲጂታዊ ቤተመጽሐፍት
- የዴንቨር የሕዝብ ቤተመጽሐፍት ታሪኮችንና ዘፈኖችን በስልክ በእንግሊዝኛ፣ በስፓኒሽኛ፣ በአማርኛ እና በቬትናምኛ የሚገኝ አገልግሎት
- የDPS' አካዳሚክ ቴክኖሎጂ ዝርዝር፡
  - የትምህርት ቤት ዝርዝሮችን (Breakdowns) → የእናንተን ት/ቤት → ሂድ ምረጡ!
  - "የወላጆች ስምምነት ያስፈልጋል" ትር፦ ግብዓቶች በወላጅ ስምምነት አማካኝነት በት/ቤታችሁ ይፈቀዳሉ
  - "የወላጆች ስምምነት ይጠየቃል" ትር፦ በዲስትሪክት የተፈቀዱ ግብዓቶች

## ለስፓኒሽኛ ተናጋሪ ወላጆች የተግባር ሀሳቦች

- Las Provincias
- Bebesymas
- Sapos Y Princesas

## ትምህርታዊ ቴቪ

PBS የተለያዩ ትምህርታዊ ቴቪ ቻናሎች አሉት። በዴንቨር አካባቢ PBSን መጠቀም የምትችሉት እንዲህ ነው።

- በአንቴና
  - Rocky Mountain PBS፦ ቻናል **6.1**
  - RMPBS KIDS፦ ቻናል **6.2**
- በኬብል ቴቪ (ኮምካስት)
  - Rocky Mountain PBS፦ ቻናል **6 እና 658**
  - RMPBS KIDS፦ ቻናል **245**
  - Create/World*፦ ቻናል **248**
  - በጥያቄ፦ ቻናል 1 ("የእርስዎ ኮሎራዶ")
- ሳተላይት (DIRECTV)
  - Rocky Mountain PBS፦ ቻናል **6**
- ሳተላይት (ዲሽ ኔትዎርክ)
  - Rocky Mountain PBS HD: ቻናል **6**